# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 182 ጥቅምት 30 2004 ገጽ 1

*ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሁለገብ ትግል የሚያምን በመሆኑ የሳይበሩን “አውድማ” በቸልታ አያይም። በሳይበር የሚደረገው ትግል የአጠቃላይ ትግላችን አንዱ አካል ነውና በተጠና እና በተደራጀ ሁኔታ መመራት አለበት ብሎ ያምናል።*

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በቢሊየኖች የሚቆጠር ሃብት ባለቤት ለመሆን የበቃው የወያኔ ኩባንያ ኤፈርት፤ የሙስና እናት እየተባለች በምትጠራው አዜእብ መስፍን ሙሉ ቁጥጥር ስር መውደቁ ተዘገበ

ወያኔ በትግራይ ህዝብ ሥም ባቋቋመውና ለጥቂት የህወሃት ባለሥልጣኖች እንደግል ንብረት እያገለገለ ያለው የ ኤፈርት ኩባንያ ስራ አስኪያጅ አባዲ ዘሙ ከሥራ አስኪያጅነቱ ተነስቶ ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ በዘረኛው ቡድን ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን እጅ መውደቁ ተዘገበ።

አዲስ ቮይስ በመባል የሚታወቀው የመረጃ አውታር እንደዘገበው፤ በህወሓት ውስጥ ረጅም ዓመታት ቁልፍ ቦታዎችን ይዞ ሲያገለግል የቆየውና የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ታማኝ የነበረው የኤፈርት ሊቀመንበር አባዲ ዘሙ ከኃላፊነቱ ተነስቶ “የሱዳን አምባሳደር” ተብሎወደ ካርቱም የተላከ ሲሆን አባዲ ዘሙ ከኃሊፊነቱ የተነሳበት ዋናው ምክንያት የሙስና እናት ተብላ ከምትጠራው አዜብ መስፍን ጋር ባለው ከፍተኛ አለመግባባት መሆኑ ታውቋል።

በበርካታ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሃብትና ንብረት በሚያንቀሳቅሰው ኤፈርት፣ የአባዲ ምክትል ሆና በባለቤቷ መለስ ዜናዊ የተሾመቺው አዜብ መስፍን፤ ሙሉ ኃሊፊነቱን ተረክባ የድርጅቱን ሪፖርት ስታቀርብ መሰንበቷንና አባዲ ዘሙም ለስሙ ያህል በሥራ አስኪያጅነት መደቡ መቆየቱ፤ የሚታወቅ ነው።

ህወሓት አዲስ አበባ ሲገባ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበረው አባዲ ዘሙ፤ ከዚያም ወደ ትግራይ ክልል ተዛውሮ የክልሉ ም/ፕሬዚዳንት ሆኖ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ከዚህም ባሻገር ከኤፈርት ሊቀመንበርነቱ በተጓዳኝ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ ሰብሳቢ ሆኖ አገልግሎአል። ይሁን እንጂ ካለፈው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ድርጅታዊ ምርጫ በኋላ፤ ከክልል ተወካዮች ም/ቤት ተመራጭነቱ እንዲነሳ መደረጉ ይታወሳል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ ነባር የከተማ ቦታ ይዞታዎችን ወደ ሊዝ ለማዞር ያወጣው አዋጅ የከተማ ነዋሪዎችን ለፖለቲካ አላማ ጭሰኛ የማድረግ እቅድ እንዳለው ተገለጸ

የከተማ ቦታን በሊዝ ለማስያዝ በሚል ድንጋጌ የወያኔ ምክር ቤት በቅርቡ ያወጣው የከተማ ቦታ አዋጅ የዜጎችን ነባር ይዞታ ለመቀማት የታሰበና ባለንበርቶች ቤታቸውን ለልጅ ልጆቻቸው ለማውረስ ያላቸውን ህጋዊ መብት የሚያሳጣ እንደሆነ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የህግ ባለሙያዎች ገልጸዋል።

ኢ-ፍትሃዊ የነበረውን የአገራችንን የመሬት ይዞታ ስርዓት በ1967ቱ ስርነቀል የመሬት ላራሹ አዋጅ የለወጠው ደርግ ፤ የከተማ ቦታን በምሪት የመጠቀም መብት ሰጥቶ ዜጎች ያላንዳች ፍርሃትና መሸማቀቅ አቅማቸው የፈቀደውን መኖሪያቤትና ንግድ ድርጅት ሲገነቡበት እንደቆዩ የገለጹት የህግ ባለሙያዎች፤ ይህ የአሁኑ የወያኔ አዋጅ ቀደም ሲል በምሪት የተያዙ ቦታዎችን ጭምር በመቀማት ወደ ሊዝ ስምሪት የሚከትና በዚህም የተነሳ ነባር ይዞታዎች ላይ ዜጎች የነበራቸውን ዋስትና የሚያሳጣ ነው ብለዋል።

አዲሱ የከተማ ቦታ አዋጅ፤ ነባር ይዞታዎች ወደሊዝ እንዲዛወሩ በግልጽ ደንግጎ እያለ፤ አዋጁ በህብረተሰቡ ውስጥ የቀሰቀሰውን ተቃውሞ ለማብረድ ሲባል የወያኔ የከተማ ቦታና የኮንስትራክሺን ሚንስቴር መኩሪያው ሃይሉ በአለቃው መለስ ዜናዊ ታዞ፤ አዋጁን ሙሉ በሙሉ በሚቃረን መንገድ እርስ በርሱ የሚጣረስ መግለጫ መስጠቱ ብዙዎችን እያነጋገረ ነው። አዋጁ እንደ ታወጀ ነባር ይዞታዎችን ወደሊዝ የማዛወሩ ተግባር እስከ 5 አመት ጊዜ ሊወስድ ይችላል ብሎ የነበረው መኩሪያው ሃይሉ ባለፈው ሳምንት በወያኔ ቁጥጥር ሥር ባለ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ቀርቦ፤ ቀደም ሲል የሰጠውን ቃል ሙሉ በሙሉ በማጠፍ አዋጁ ነባር ይዞታን እንደማያካትት ለመናገር ሞክሮአል። የወያኔው ሹመኛ መኩሪያው ሃይሉ የሰጠው የተምታታ መግለጫ የሚያመለክተው፤ ከአቅም በላይ የሆነው የኑሮ ውድነትና የመልካም አስተዳደር ጉድለት በፈጠረው የውስጥ ለውስጥ ህዝባዊ ተቃውሞ ላይ ተጨማሪ ነዳጅ በመሆን የህዝብ ቁጣ ሊቀሰቅስ ይችላል ተብሎ ስለተሰጋ ህዝብን ለማረጋጋት የተዘየዴ እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ።

ወያኔ በመላው አገሪቱ የገጠር መሬት ላይ የሚኖሩትን ዜጎች የራሱ ጭሰኛ የሚያደርግ ፖሊሲ በማውጣት አዝዙን የማይደግፉትን ለዘመናት ከኖሩበት ቄያቸውና የእርሻ ማሳቸው እያፈናቀለ፡ የፖለቲካ ድጋፍ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የጀርመን የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አባላት ሃገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የረጂም ጊዜ ግንኙነት እየተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት በቸልታ እንድንመለከት የሚያደርገን አይሆንም አሉ

የጀርመን ፓርላማ ምክር ቤት አባላት በቅርቡ በኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉብኝት አስመልክቶ ከትናንት በስቲያ 09.11.2011 በሰጡት መግለጫ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የረጂም ጊዜ ግንኙነት በአገሪቱ እየተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እያየን ዝም እንድንል የሚያደርገን አይደለም አሉ።

በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጉብኝት ያደረጉት የሊበራል ፓርቲ ተወካዩዋ ወይዘሮ ማርቲና ሹስተር በጉብኝታቸው ወቅት ያስተዋሉትን እውነታ ሲገልጹ “ህግ ይፈቅድልኛል እያሉ አንድን ሰው ያለወንጀሉ በዘፈቀደ ማሰር ፈጽሞ አይቻልም” ያሉ ሲሆን የኢትዮጵያው አገዛዝ አዲስ ባወጣው የፀረ-ሽብር ህግ ሽፋን ከመንግስት የተለየ አስተሣሰብ የሚያራምዱና በስርዓቱ ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ሁሉ በግፍ እያሰረ ነው ብለዋል።

“በኢትዮጵያ እየሆነ ያለው ነገር እኛን ሊበራሎቹን እጅግ ያሣስበናል”ያሉት ወይዘሮ ሹስተር፤ በአገሪቷ ለጋዜጠኞች፣ ለተቃዋሚዎችና ለኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ያለው ነፃነት ወደ ፊት ከመሄድ ይልቅ፤ ወደ ሁዋላ ተመልሶ ቀጭጮ ቀርቷል በማለት ተቃዋሚዎችና ጋዜጠኞች በህግ ሽፋን እየታሰሩ መሆናቸውን እንዳረጋገጡ አመልክተዋል።

ወይዘሮ ማርቲና ሹስተር “ማስፈራራት በአገሪቷ ላይ ነግሷል። ያነጋገርኳቸው የተቃዋሚ ፓርቲ ድርጅቶች ሌላው ቀርቶ የሚገናኙበትና የሚሰባሰቡበት እንኳ ቢሮ የላቸውም። የመንቀሳቀሻ ገንዘብና የመገናኛ መስመርም እንደዚሁ የላቸውም። ከሁሉም በላይ መንግስት እየሰራ ስላለው ሥራ ለመጠየቅ፣ለመወያየትና ለመነጋገር ምንም ዓይነት ዕድልና መንገድ የላቸውም” ሲሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የፀረ ሽብር ህግ ከሌሎች አገሮች የፀረ-ሽብር ህግ የተለየ እንደሆነ የጠቆሙት ተወካዩዋ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ታስቦ የወጣውም ህግ እንዲሁ በአገሪቱ ዲሞክራሲን ለማስፈን የሚደረግን ሙከራ የሚያደናቅፍ እንደሆነ ለህዝብ እንደራሴ ምክር ቤት አባላቱ ገልጸዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በቤልጂዬም የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የኢድ-አልፈጥርን በዓል በደማቅ ሁኔታ አከበሩ። በበዓሉ ላይ ተጋብዘው የነበሩት በቤልጂዬም የወያኔ ኤምባሲ ሰራተኞች የግንቦት7 አመራር አባል ባለበት ቦታ መገኘት ያስጠይቀናል ሲሉ አዳራሹን ጥለው ፈረጠጡ

ዕሁድ ጥቅምት 26 ቀን ተከብሮ የዋለውን የኢድ-አልፈጥርን በዓል በቤልጂዬም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች አንድ ላይ በመሰባሰብ በደማቅ ሁኔታ ማክበራቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ሪፖርት ገለጸ።

በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በየአመቱ በደማቅ ሁኔታ በሚከበረው በዚህ ታላቅ መንፈሳዊ ሥነሥርዓት ላይ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች መካከል እልቂት ሊያስነሳ የሚችል ክፍፍል ሆን ብሎ እየፈጠረ መሆኑን በድምጽና በቪዲዮ ማስረጃ የተደገፈ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቦበታል።

በቤልጂዬም የሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ በዚህ በአል አከባበር ላይ ተገኝቶ የሙሲሊሙ ህብረተሰብ የተሰማውን ቅሬታና ስጋት እንዲያዳምጥ በቤልጂዬም የሉቁማን ኢትዮጵያዊያንና ቤልጂየማዊያን ሙስሊሞች ማህበር ጋብዞት እንደነበረና በግብዣውም መሰረት ከኤምባሲው 3 ተወካዮች ተልከው የምሳ ግብዣው እስኪጠናቀቅ ድረስ በቦታው እንደነበሩ የደረሰን ዘገባ አመልክቶአል። ሆኖም የምሳ ሥነስረዓቱ አብቅቶ በበአሉ ላይ የተጋበዙት እንግዶችና ምዕመናን በተዘጋጀው አዳራሽ ውስጥ ቦታ ቦታቸውን መያዝ እንደጀመሩ በዓሉን ለማክበር በግል የተጋበዙት የግንቦት 7 አመራር አባል እስፍራው በመድረሳቸው 3ቱም የወያኔ ተላላኪዎች እርስ በርሳቸው በጆሮ ከተንሾኳሾኩ በኋላ አዳራሹን ለቀው እንደወጡ ለማወቅ ተችሎአል።

በአገሩ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 7 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ይከሄዳል በተባለው በዚህ የኢድ አልፈጥር በአል ላይ ለመሳተፍ መጥቶ የነበረው የወያኔ ኤምባሲ ቡድን ዋናው የበዓሉ ዝግጅት ሊጀመር ሲል አዳራሹን ጥሎ በመውጣቱ የተገረመው ምዕመንና ግብዣ የተደርገላቸው እንግዶች ወደ ኋላ እንዳረጋገጡት፤ መንግሥታቸው ሽብርተኛ ብሎ ከፈረጃቸው ፓርቲ አመራር አባል ጋር በአንድ መድረክ መሳተፍ ሊያስጠይቃቸው እንደሚችል ስጋት ገጥሞአቸው ጥለው ለመውጣት እንደተገደዱ ለአስተባባሪዎቹ መግለጻቸውን ለመረዳት ተችሎአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ትኩረት በሳይበር ለሚደረገው ትግል!!!

ባለንበት የመረጃ ዘመን፤ ሳይበር (ለምሳሌ ኢንተርኔት) ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ትግል ከሚደረግባቸው አውድማዎች አንዱ ሆኗል። ለሰሜን አፍሪቃና መካከለኛ ምሥራቅ ህዝባዊ አብዮቶች ኢንተርኔት ስለተጫወተው ሚና ብዙ የተባለ ስለሆነ እዚህ ላይ ደግሞ ማንሳት አያስፈልግም። መረሳት የሌለበት ሃቅ ግን አምባገነኖችም ይህንን ስለሚያውቁ እነሱም የሚዘጋጁበት መሆኑ ነው። የዘመናችን አምባገነን መንግሥታት የምድር፣ የባህርና የአየር ኃይሎቻቸውን ከማፈርጠም ጎን ለጎን "የሳይበር ኃይላቸውን" ማጎልበት የሥራቸው አንድ አካል አድርገውታል። ሳይበር የስለላ ስራዎቻቸውን የሚያቀላጥፉበት መስክ ከሆነ ውሎ አድሯል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝም "ለሳይበር ጦርነት" በርካታ ሠራዊትና በጀት እንደመደበ ለግንቦት 7 የሚደርሱት መረጃዎች ያረጋግጣሉ። መለስ፣ መደበኛ ሥራቸው የሬድዮና የቴሌቪዥን ሞገዶችን ማወክ፤ ለዲሞክራሲ ወገንተኛ የሆኑ ድረገፆችን መዝጋት፤ በግለሰቦች ኮምፒዩተሮች ውስጥ የተቀመጡ ፋይሎችን መስረቅ፤ የግለሰቦችንና የድርጅቶችን የኤሌክሮኒክስ ፓስታዎችን (ኢሜሎችን) መጥለፍ እና የመሳሰሉ እኩይ ተግባራትን ማከናወን የሆነ በርካታ "ባለሙያዎችን" አሰማርቷል።

ለዚህ ምላሻችን ምንድነው?

በውጭ አገራት ያሉ ኢትዮጵያዊያን በፓልቶክ የመወያያ ክፍሎች፣ በድረገፆች፣ በዩ ቱዩብ እና ፌስ ቡክ አማካይነት ስለአገራቸው ጉዳዮች ሲወያዩና መልዕክቶችንም ሲያስተላልፉ ቆይተዋል፤ አሁንም በማስተላለፍ ላይ ናቸው። በዚህ ረገድ ሊወደሱና ሊበረታቱ የሚገባቸው ፓልቶኮች፣ ድረገፆችና ፌስ ቡኮች አሉ። ሆኖም ግን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከሚያደርስብን ጥቃት እና ለነፃነታችን ማድረግ ከሚገባን አንፃር ሲታይ እስካሁን እየተደረገ ያለው ጥረት እጅግ አነስተኛ ሆኖ እናገኘዋለን።

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሁለገብ ትግል የሚያምን በመሆኑ የሳይበሩን "አውድማ" በቸልታ አያይም። በሳይበር የሚደረገው ትግል የአጠቃላይ ትግላችን አንዱ አካል ነውና በተጠና እና በተደራጀ ሁኔታ መመራት አለበት ብሎ ያምናል።

እንደ ማንኛውም የትግል መስክ "የሳይበር ጦርነትም" የተጠና ስትራቴጂ፣ ሰውና ድርጊት ይፈልጋል። እናም ራሳችንን በእነዚህ ሶስት አቢይ ምሰሶዎች አንፃር መመርመር ይገባናል ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

የኢሌክትሮኒክስ፣ የኮምቲዩተርና የሶፍት ዌር እውቀት ያላቸው ለነፃነትና ለፍትህ የቆሙ ኢትዮጵያዊያን የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንስተው፣ ተወያይተውባቸው ምላሽ ቢሰጧቸው እና ተግባራዊም ቢያደርጓቸው ትግላችን ጉልህ በሆነ መንገድ ያግዛሉ ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

ስትራቴጂን በተመለከተ

- በሳይበር ከሚደረግ ትግል ማግኘት የምንችለው ውጤት ምንድነው?
- እምንፈልገው ግብ ለመድረስ ምን ዓይነት አማራጭ መንገዶች አሉን?
- የሳይበር ትግል ከሌሎች የትግል ዓይነቶች ጋር እንዴት ይቀናጃል?

በሳይበር ዘርፍ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምንድናቸው?

ሰውን በተመለከተ

- በሳይበር ትግል የሚሳተፉ ወገኖቻችን እንዴት ቢደራጁ ይሻላል?
- እንደምን ያለ አደረጃጀት ነው ለዚህ የትግል ዘርፍ ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው?
- ባለሙያዎችን ወደዚህ የትግል ዘርፍ ለመሳብና አዳዲስ ባለሙያዎችን ለመፍጠር ምን ማድረግ እንችላለን?

ድርጊትን በተመለከት

- በሳይበር ዓለም ውስጥ እንዲደረግ የምንፈልገው ተግባር ምንድነው?
- እያንዳንዱ "የሳይበር አርበኛ" ጊዜውንና እውቀቱን ሰውቶ ውጤት በሚያመጣ የሳይበር ተግባር ላይ እንዲያተኩር ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
- እቅዶቻችን በሥራ ላይ መዋል አለመዋላቸው እንዲሁም የምንፈልገው ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸው እንዴት መከታተል እንችላለን?

የተናጠል ሙከራዎችን እንደምን ማቀናጀት እንችላለን?

የሚሉና ተመሳሳይ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ ሊያገኙ ይገባል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝን የኢንተርኔት አፈናና ስለላ ከመቋቋም ጀምሮ የአፀፋ ምላሽ እስከመስጠት የዘለቀ በሳይበር ግንባር መከወን ያለባቸው በርካታ ተግባሮች አሉ። አደረጃጀቱ ይለይ እንደሆነ እንጂ እንደሌሎቹ የትግል ዘርፎች ሁሉ መደራጀት በዚህም ግንባር ወሳኝ ነው።

ስለሆነም የኤሌክትሮኒክስ፣ የኮምፒዩተርና የሶፍትዌር እውቀትና ዝንባሌ ያላቸው ወገኖቻችን ጊዜያችሁ እና እውቀታችሁ ትግሉን በሚያግዙ ተግባራት ላይ እንድታውሉ፤ ሥራዎችንም በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ እንድትሠሩ ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጥሪ ያደርጋል። ለዚህ ተግባርም ባለሙያዎች ተሰባስባችሁ የምትመክሩበት መድረክ በአስቸኳይ እንድትፈጥሩ ግንቦት 7 ወገናዊ ጥሪ ያቀርብላችኋል።

እውቀታችንና ጊዜያችንን አስተባብረን ከተነሳን የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ የሚፈጽመፈውን የሳይበር አፈና ከመቋቋምም አልፈን የአፀፋ ምላሽ መስጠት እምንችልበት ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለን ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

አፈና በተገኘበት መስከ ሁሉ እንዋጋዋለን፤ ትግላችን ሁለገብ ነው!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

---

## ከፋፋዩ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን ማጋጨቱን ቀጥሉአል፣ ግጭቱን ወደ ከፋ ደረጃ ለማድረስ "አህባሽ" ለተባለው ቡድን ወታደራዊ ስልጠና እየሰጠ መሆኑ ታወቀ

ኢትዮጵያዊያንን በሰበብ አስባቡ በመከፋፈልና በማበጣበጥ ራሱን ስልጣን ላይ የማቆየት አባዜ የተጠናወተው ከፋፋዩ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን ማጋጨቱን እንደቀጠለ ሲሆን ግጭቱን ወደ ከፋ ደረጃ ለማድረስ "አህባሽ" ለተባለው ቡድን ወታደራዊ ስልጠና እየሰጠ መሆኑ ከአገር ውስጥ አልፎ በውጪ አገር የሚኖሩትንም ሙስሊም ህብረተሰብ እጅግ እያሳሰበና እያስቆጣ መሆኑ ተገለጸ።

በተለያዩ የአውሮጳ፤ የሰሜን አመሪካና ኤዥያ ከሚኖሩ የሙስሊም ኮሚኒቲዎች ጋር የጋራ ህበረትና ትብብር እንዳለው የተገለጸው የሉቅማን ኢትዮጵያዊያን ቤልጂማውያን ሙስሊሞች ማህበር ሊቀመንበር የሆኑት አቶ አብዩ ያሲን እሁድ ጥቅምት 26 ቀን በብራስልስ ከተማ ለ1 ሺ 4 መቶ 33ኛው ጊዜ የተከበረውን የኢድ አል አድሃ አረፋ በዓል ምክንያት በማድረግ ለተሰበሰበው ምዕመንና ተጋባዥ እንግዶች ባደረጉት ንግግር ይህንን የሙስሊም ህበረተሰብ ስጋት በማስረጃ አስደግፈው አቅርበዋል።

የሙስሊሙን ህበረተሰብ ለመከፋፈል "መንግሥት" ግልጽ የሆነ ዘመቻ እያካሄደ ነው ያሉት አቶ አብዬ ፤ ክሳቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ከባህር ማዶ የተላኩ የአህባሽ እምነት ተከታዮች የእምነታቸውን ዘርፍ አገር ውስጥ ለማስፋፋት እንዲችሉ 800 ለሚሆኑ ሰዎች ሀረር ውስጥ ቀናትን የፈጀ ስልጠና እንደተሰጠና ወደ ሌሎች ክልሎችም ተሰራጭተው ትምህርት ሊሰጡ የሚችሉ 200 ተጨማሪ ሰልጣኞች በአሁኑ ሰዓት በሰንዳፋ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ውስጥ እየሰለጠኑ እንደሚገኙና ስልጠናውንም እንደጨረሱ እስከ 30 ሺ የሚጠጉ ሙስሊሞችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሰልጠን ብቃት ይኖራቸዋል የሚል እቅድ መዘርጋቱን በመንግሥት ተወካዮች መነገሩን በማስረጃ አስደግፈው አስረድተዋል።

አቶ አብዩ ያሲን፣ በዚሁ ንግግራቸው አህባሽ የተባለው አስተምህሮ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም አስጊ መሆኑን ገልጸው የወያኔው ኢህአዴግ አገዛዝ የአገር አንድነትን አደጋ ላይ የሚጥል፣ የእርስ በርስ ግጭቶችን ሊፈጥር የሚችል እምነት ለመደገፍ ለምን እንደተነሳሳ ግራ እንደገባቸው አልሸሸጉም። አቶ አብዩ በማብራሪያቸው የወያኔው አገዛዝ በህገመንግስቱ የሰፈሩትን መብቶች መርገጡን ጠቅሰው፣ አሁን የሚታየው አንዱን አስተምህሮ ደግፎ ሌላውን የማውገዝ አካሄድ የአገርን ሉአላዊነት የሚጎዳ፣ ህዝቦች ለዘመናት ተቻችለው የኖሩበትን ስርአት የሚያጠፋ፣ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ያላቸውን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት፣ የሙስሊሞችን እና የእስልምናን መልካም ምስል የሚያበላሽ በአጠቃለይ በአጼው ዘመን ወደ ነበረው ታሪክ መልሶ የሚወስድ መሆኑን ተናግረዋል። በመጨረሻም ሊቀመንበሩ በንግግራቸው አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዩውን አደገኛ ሁኔታ መቀዬር የሚቻልባቸውን መንገዶችም ዘርዝረዋል።

በሌላ በኩል በበአሉ ላይ ከተገኙት ሙስሊሞች መካከል አቶ ገአዝ አህመድ የተባሉት የቤልጂየም ነዋሪ፣ የአህባሽ መሪዎች አስተምህሮውን በአገር ውስጥ እንደማንኛውም የእምነት ተቋም ለማስፋፋት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሙብት ጉዳይ በመሆኑ እንደማይቃወሙት ገልጠው፣ ይሁን እንጅ የወያኔ ኢህአዴግ ከፋፋይ አገዛዝ በፖሊሲ ደረጃ ቀርጾ፣ በጀት መድቦና ሰዎችን አሰልጥኖ እምነቱን ለማስፋፋት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እርሳቸውም ሆኑ ሌሎች ሙስሊሞች እንደማይቀበሉት ተናግረዋል።

## ጣዖቱን ተቃወሙት መሰዊያውንም አፍርሱት!

ወያኔ ብሶት የወለደው የህዝብ ልጅ ነበር። አሁን ያ የህዝብ ብሶት የወለደው ድርጅት ሙቶ በቀበሩ ላይም መለስ ዜናዊ የሚባል ጣኦት ቁሟል።ኢትዮጵያዊያንም ለዚህ ጣኦት መስዋእት ሁነው ቀርበውለታል። ጣኦቱም በፈለገው መንገድ የቀረበለትን መስዋእት እየበለተ ምሱን እየወሰደ ነው።

ይህ ጣኦት ይሁን ያለው እየሆነ አይሁን ያለው ደግሞ ሳይሆን እየቀረ እነሆ ሁለት አስርተ ዓመታት ተቆጠረ።

ይህ ክፉ ጣዖት አማራና ኤምፔሪያሊዝም የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ናቸው ብሎ እኩይ ስብከቱን ጀመረ። ልቦናቸው ከባህር ዓለት በላይ የጠነከረው ካዳሚዎቹም ስብከቱን ሰምተው የወንድሞቻቸውን ደም በከንቱ እያፈሰሱ መኖርን ልማድ አድርገው ለሁለት አስርተ ዓመታት ዘለቁ። ድሃ አማራ እንደምን ሁኖ ጠላታችን ይሆናል? ኤምፔሪያሊዝምስ ማን ነው? ብለው የጠየቁ ደጋግ ትግሬዎችን አድሃሪ ብለው ብዙ መከራ አደረሱባቸው።አንዳንዶቹን በእሳት አቃጥለው ለጣዖቱ መስዋእት አቀረቡለት። አንዳንዶቹንም በደረግ ጥይት አስመትተው ደማቸውን አስፈሥሰው ሌላ መስዋእት አደረጓቸው። ሌሎችንም ከቀያቸው እንዲሰደዱ አድረገው ለመከራ ዳረጓቸው።

ይህ ክፉ ጣኦት የደስታው ምንጭ በወንድማማቾች መካከል የሚነሳው ግጭት ነው። እስከ አሁን ብዙ ግጭቶች ተፈጥረው ብዙ ደሙ ፈሷል።ጣኦቱም የወንድሞች ደም ሲፈስ ረክቶ ክፋቱን አጠናክሮ ቀጥሎበታል። ይሁን እንጂ ጣዖቱ መለስ ዜናዊ የትላልቆቹን ብሄረሰብ አባላትን ደም ለማፋሰስ የቋጠረው ሁሉ በሚፈልገው ሁኔታ አልያዘለትም። ይህ እኩይ ሙከራው በህዝቦች አርቆ አስተዋይነት እየመከነበት ነው። መለስ ዜናዊ ግን የማያባራ ጥፋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ክሮችን መምዘዝ ጀምሯል። በአማራና በኦሮሞ መካከል ሊገነባ የሞከረው የጠብ ግድግዳ እየተናደ ሲመጣ ዓይኑን ወደ ሃይማኖቶች አዘንብሏል። በዚህ ወጥመድ ውስጥ የሚገቡ የዋሃን አማኞች እንደማይጠፉ ጣኦቱ መለስ ዜናዊ ጠንቅቆ ያውቃል።

ዛሬ በነጻው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የዘርን ግድግዳ ሰብረው በአንድ ጣሪያ ሥር ቁጭ ብለው ስለ ነጻነታቸው ማውራት መቻላቸው መለስ ዜናዊን አስደንግጦታል።እንደጠላት እንዲተያዩ ሲደረጉ የነበሩ ህዝቦች የለም እኛ ወንድማማች እንጂ ጠላት አይደለንም ብለው እጅ ለእጅ ተያይዘው መቆም መጀመራቸው ለጣኦቱ የሚቀርብለትን የደም መስዋእትነት ስለሚያቆመው መለስ ዜናዊ ክፉኛ ተሸብሮ የሃይማኖት ግጭቶችን እዚህና እዚያ እየፈጠረ ነው።

በአገራችን ታሪክ እስላምና ክርስትያን ተከባብሮ በክፉም በደጉም እየተገናኘ ለብዙ ዘመን አብሮ የኖረ ህዝብ ነው።ይህን አብሮነት ለማፍረስ መለስ ሆን ብሎ የሚያደርጋቸው ተንኮሎችን በተደጋጋሚ ተመለከተናል። አስቀደሞ በታሰበበት ሁኔታ በጎንደር ከተማ አንድን ቦታ ለመስኪድም ለቤተክርስትያንም መስሪያ እንዲሆን ለሃይማኖት ተቋማቱ በመስጠት ግጭት እንዲፈጠር አድርጎ የወንድማማቾች ደም እንዲፈስ አድርጓል። ወደ ደቡብም በመዝለቅ በአሰንዳቦ ከተማ በክርስትያኖችና በሙስሊሞች መካከል ግጭት ተፈጥሮ የብዙ ዜጎች ደም ፈሷል።ይህም በጣኦቱ መለስ ዜናዊ ካዳሚዎች አማካኝነት ሆን ተብሎ የተፈጠረ ግጭት መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

የጎንደረም ሆነ የአሰንዳቦ ህዝብ ከመሬት ተነስቶ እርስ በርሱ የሚገዳደልበት ምንም ምክንያት የለውም። ጣኦቱ መለስ ዜናዊ ህዝቡ ተስማምቶ ሲኖር የደነግጣል ይሸበራል። ነፍሱም ሠላም ታጣለች። በአሰንዳቦ ከተማ ቅዱስ ቁርዓንን ቀዳድዶ በክርስትያኖች መንድር በመጣል ያንንም ራሱ ለፈጠራቸው ሙስሊም መሰል ካድሬዎች በማሳየት ጠብና አምባጓሮ እንዲነሳ አድርጎ የወንድማማቾችን ደም አፋሷል። ጣኦቱ ይሁን ያለውን ለማስፈጸም በየቦታው ያሉ ነውራቸው ክብራቸው የሆኑ የጣኦቱ ካዳሚዎችም የሚገነቡትን የጠብ ግድግዳና የሚያስከትለውን መዘዝ ሳይረዱ የዜጎችን ንጹህ ደም እያፈሰሱ መስዋእት ለማቅረብ ሌት ተቀን እየተጉ ነው።

የተከበራችሁ የአገራችን ዜጎች ዛሬ ሃይኖታችን የመለያያችን ምክንያት ሊሆን አይገባም። ሃይማኖት መገለጫው ፍቅር እንጂ የወንድምን ደም ማፍሰስ አይደለም። መለስ ዜናዊ ሆን ብሎ በሃይማኖቶች መካከል የሚፈጥረው ሰሃ በህዝቦች መካከል ሥር ሰዶ በቅሎና ፍሬ አፍርቶ ክፉ ዘር እንዳይፈጠር ከማስተዋል ጋር የመለስን ሰይጣናዊ እኩይ ሥራዎችን እንቃወም። የወንድሞቻችሁን ደምም መስዋእት አድረገው ለጣኦቱ እድሜ መርዘም በየግዜው ለማቅረብ የሚተጉትን በቃ እንበላቸው።

ኢትዮጵያችን ሁሉም ዓይነት ሃይማኖቶች ተከባብረው የሚኖሩባት የሁሉም አገር ነች። ኢትዮጵያዊያን በሃይማኖታቸው ምክንያት የመገዳደል ልማድ ኑሯቸው አያውቅም። በሃይማኖት ምክንያት ወደ ግጭት የሚወስዱን የሰው ልጆች ደም ምስ የሆናቸው እነ መለስ ዜናዊ ናቸውና አንድ ላይ ሁነን የዘመናችንን ይህን ክፉ ጣዖት እንቃወመው። የመሰውያውንም ሥርዓት ለማፍረስ በአንድ ላይ እንቁም።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!

---

## በብዙ ሚሊዮኖች ዶላር ወጥቶበት እንዲታተም በተደረገው የስምንተኛ ክፍል የስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት መጽሀፍ ውስጥ "ተማሪዎችን ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ጽሁፎች ተካትተዋል" በሚል ምክንያት፣ ተማሪዎችና መምህራን የመጽሀፉን አንዳንድ ገጾች ቀደው እንዲያቃጥሉ ታዘዙ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ከሪፖርተሮቹ የደረሰውን መረጃ ዋቢ በማድረግ እንደዘገበው በውጪ ምንዛሪ በውድ ዋጋ ታትመው ወደ አገር ቤት የገቡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ መጻህፍት ለተማሪዎችና መምህራን ከተከፋፈሉ በኋላ ነበር ባለሥልጣናቱ ይህንን ውሳኔ ያስተላለፉት። ይሁን እንጂ መጽሀፉ ባለፈው መስከረም ወር በሚታደልበት ጊዜ ተማሪዎች መጽሀፉን ቀድደው ቢገኙ 100 ብር እንደሚቀጡ በመምህራን በኩል ተነግሮአቸው እንደነበር ታውቆአል።

የአማራ ክልል ባለስልጣናት ተማሪዎችና መምህራን የመጽሀፉን ገጽ 103 እና 104 እንዲቀዱ ሲያዝዙ፣ ተማሪዎችና መምህራን "ይህን መጽሀፍ ብትቀዱ 100 ብር ትከፍላላችሁ ብላችሁናልና በአዋጅ መጽሀፉን ቅደዱ ተብሎ እስካልተነገረን ድረስ፣ ነገ ደግሞ መጽሀፉን ቀዳችሁዋል በሚል ልንከሰስ ስለምንችል አንከፍልም "የሚል መልስ በትምህርት ቤት ርእሳነ መምህራን አማካኝነት ልከዋል።

በሁኔታው ግራ የተጋቡት ባለስልጣናት መጽሀፉ በጅምላ እንዲሰበሰብ እንዲደረግ መመሪያ ካወረዱ በሁዋላ፣ በምእራፍ 10፣ ገጽ 103 እና 104 የሰፈሩት ጽሁፎች ተቀደው እንዲቃጠሉ ተደርጓል።

"ተውለደሬ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሰፈር" በሚለው ምእራፍ ስር ተውለደሬ እና ኩሸሽሌ የተባሉ ሁለት ወረዳዎችን በመልካም አስተዳዳር እና በዲሞክራሲያዊ ስርአት ያላቸውን ልዩነት ያብራራል። የሁለቱን ወረዳዎች ልዩነት ለማነጻጸርም አቶ አልቃድር አማን የተባሉ የመቂት ወረዳ ተወላጅ በእማኝነት ቀርበዋል።

አቶ አልቃድር ለ26 አመታት በውጭ አገር ከኖሩ በሁዋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው በኩሸሺሌ ወረዳ ውስጥ ስራ ለመስራት ፈልገው ሙስናውና ቢሮክራሲው አላሰራ ስላላቸው ስራቸውን ወደ ተውለደሬ በማዞር ለመስራት መገደዳቸውን ጽሁፉ ይገልጣል ።

በገጽ 104 ላይ ደግሞ "ዲሞክራሲ ባልሰፈነበት አገር መከባበር መተማመን መደማመጥ አይኖርም፣ ይልቁንም የጥቂቶች አምባገነንነት ስለሚደነድን የብዙሀን መጎዳት የማይቀር ነው። ብዙሀኑ ለጋር እድገት የሚያደርጉት መነሳሳት ይቀጭጫል። ማህበራዊ ልማትም ይጠፋል። በተቃራኒው ግን የዲሞክራሲ ስርአት መገንባት ተከታትሎም የጋራ መግባባት መፈጠርና የመልካም አስተዳደር መስፈን ማህበራዊ ፍትህ እንዲመጣና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲከተል ስለሚያደርግ አገር ይበለጽጋል። የጋራ መግባባትና የመልካም አስተዳደር መስፈን መልሶ ዲሞክራሲውን ስለሚያጠናክር እድገቱ ቀጣይነት ይኖረዋል። እነዚህ ውጤቶች ግን በራሳቸው የሚመጡ አይደሉም። በህብረተሰቡ ውስጥ እነዚህ ውጤቶች እውን እንዲሆኑ የሚያደርግ ጠንካራ ንቁ ተሳትፎ ያስፈልጋል። ያለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ተጠናክሮ አይገነባም፣ መልካም አስተዳዳርም በዘላቂነት ሊሰፍን አይችለም። እነዚህ ባልተሟሉበትም ልማትና መልካም አስተዳደር ሊሰፍን አይችልም" የሚል ሰፍሯል።

ለገጾች መቀደድ ዋና መክንያት የሆነው "ዲሞክራሲና መልካም አስተዳዳር ባልሰፈነበት የኩሸሺሌ ወረዳ ነዋሪ ብትሆን ምን እርምጃ ትወስዳለህ?" የሚለው ጥያቄ በርካታ ችግሮችን ይዞ የሚመጣ በመሆኑ ነው በማለት በደቡብ ጎንደር መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት አቶ አበባው አለፈ ለኢሳት ተናግረዋል ተብሎአል።

አገዛዙ በአገኘው አጋጣሚ ሀሉ ስለመልካም አስተዳዳርና ዲሞክራሲ እንዳይነሳበት ጥረት እንደሚያደርግ የገለጡት አቶ አበባው፣ ብዙ ሚሊዮኖች ፈሶበት እንዲሰራጭ የተደረገው መጽሀፍ እንደገና እንዲታተም ሊደረግ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የመጽሀፉን የመጀመሪያ ቅጅ ያዘጋጁት አቶ ሸዋ ቀና ቸርነት፣ አቶ ቦጋለ ስብሐቱ፣ አቶ አሰግደው ተስፋዬ፣ አቶ ተስፋዬ ክፍሉ፣ አቶ ጌታቸው በለጠ፣ ወ/ሮ ጸሀይ መላኩ፣ ወ/ሮ ውዳላት ገዳሙ፣ ወ/ሮ ዬዝና ወርቁ፣ ወ/ሮ አገረደች ጀማነህ፣ አቶ ብቃለ ስዩም እና አቶ የሻው ተሰማ ናቸው።

ኢሳት በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች በሲቪክ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የኢህአዴግን ፖሊሲ የሚተች አስተያየት ሲያቀርቡ በካድሬ መምህራን ተጠርተው እንደሚጠዬቁ መዘገባችን ይታወሳል።

## አሸባሪው የወያኔ አገዛዝ አሻንጉሊት ፍርድ ቤት፤ በሽብርተኝነት ስም የታሰሩ የስዊድን ጋዜጠኞችን ክስ ውድቅ ሲያደርግ በሁለቱ የኦብነግ አባላት ላይ መፍረዱ አገዛዙ ያለበትን ከፍተኛ ጭንቀት አመላካች ነው ተባለ

ከሁለቱ ስዊድናዊያን ጋራ በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሦስተኛ ወንጀል ችሎት በዋና ወንጀል አድራጊነት የተከሰሱት የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) አባላት የሆኑት አብዲወሊ መሐመድ እስማኤል እና ከሊፍ ዐሊ ዳሂር የ17 ዓመት ጽኑ እሥራት ሲፈረድባቸው የስዊድን ሃገር ጋዜጠኞች ክስ ግን በቂ መረጃ አልተገኘም በሚል የቀረበባቸው ክስ ውድቅ መሆኑ ታወቀ:: በእለቱ የፍርድ ቤቱን ታዳሚዎች ያስገረመው ነገር የወያኔው አሻንጉሊት ፍርድ ቤት ዳኞች የፍርዱ ዓላማ ጥፋተኛውን ማስተማር፣ ኅብረተሰቡን እና አገርን ደግሞ ከጥቃት መከላከል በመኾኑ ወንጀሉን በመካከለኛ ደረጃ መድበነዋል ማለታቸው እንደሆነ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ አመልክቱአል::

አጭበርባሪው የወያኔ አገዛዝ እየሰራ ያለውን የማፊያ አይነት ተግባር አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት ዘጋቢያችን የጠየቃቸው የፍርድ ሂደቱን የተከታተሉ ሰዎች እንደገለጹት፣ ወያኔ ከምእራባዊያን ያለበትን አስፈሪ ጫና ላለመጋፈጥ ብሎም ደግሞ ፍርድ ቤቱ በስርአት እየተመራ ያለ ህጋዊ ፍርድ ቤት ነው እንዲባልለት በማሰብ የስዊድን ጋዜጠኞችን ክስ ውድቅ ሲያደርግ ንጹሃን አርብቶ አደር ዜጎችን ግን በግፍ እንዲህ አይነት ፍርድ እንዲሰጥባቸው አድርጉአል።

ወያኔ ሥልጣን ላይ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የፖለቲካ ባላንጣዎቹን በፍትህ ሥም ከርቼሌ ለመወርወር እንዲያስችለው የራሱን የፖለቲካ ሪዮት የሚከተሉትንና በጥቅምና በሙስና ተባባሪ የሆኑትን ሰዎች ስቪል ሰርቪስ ኮለጅ እያስገባ አስመርቆ በዳኝነትና በአቃቤ ህግነት በመሾም ተመሳሳይ ግፍ በመፈጸም ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

### በቢሊየኖች የሚቆጠር ሃብት ባለቤት ለመሆን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ከሕወሓት ክፍፍል በኋላ በድርጅቱ ውስጥ ከቀሩት የህወሓት አመራር አካላት መካከል የመለስ ቁልፍና ታማኝ የነበረው አባዲ ዘሙ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከሙስና እናት አዜብ ጋር የፈጠረውን አለመግባባት ተከትሎ በውለታ ቢሱ መለስ- ፊት ተነስቶ እንደነበር ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በህገወጥ መንገድ መቆጣጠሩ እና ከህግ በላይ መሆኑ በስፋት የሚታማው ኤፈርት ሙሉ በሙሉ በአምባገነኑ መለስና በባለቤቱ ቁጥጥር ስር የመውደቁ ጉዳይ፤ በእነ ስብሃት ነጋና በርካታ የሕወሓት ባለስልጣናት ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ መፍጠሩ ይሰማል። በሕወሓት ባለስልጣናት መካከል መቃቃርና ክፍፍል እየሰፋ መምጣቱንም፤ ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ።

የሙስና እናት የሆነቺው አዜብ መስፍን በህወሀት ማዕከላዊና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት፣ በወያኔ ኢህአዴግ ማዕከላዊና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት፣ በምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢነት፣በብሔራዊ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት የቦርድ ሰብሳቢነት፣ በኢፈርት ሥራ አስኪያጅነትና በሌሎች በርካታ የስልጣንና የሹመት ቦታዎች ተመድባ ያለች ያለችሎታዋና አቅሟ ድርብርብ ሥልጣን ተሰጥቶአት የአገሪቱን ሃብት እየቦጠቦጠች ያለች የዘመናችን ጉድ ሴት ነች።

### ወያኔ ነባር የከተማ ቦታ ይዞታዎችን ወደ ሊዝ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለሚሰጡትና በካድሬነት ለሚያገለግሉት ሲሰጥ እንደኖረ የሚናገሩ የፖለቲካ ተንታኞች፤ በዚያ እፍትሃዊ አሰራር የገጠሩን ህዝብ ምርኮኛ አድርጎ የፖለቲካ ድጋፊ ማግኘት የተሳነው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ፤ ይባስ ብሎ ምንም አይነት የድጋፍ መሠረት በሌለው የከተማ ክልል ነዋሪዎች ላይ ይህንን አዲሱን አዋጅ በማወጅ በቀጥታ ጭሰኛው ለማድረግ ፈልጎና አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ያመለክትላ ይላሉ።

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ጀምሮ እስከ ምርጫ 97 ድረስ በነበሩት አመታት አብረውት ከጫካ ለመጡት አብዛኛው የህወሃት ታጋዮች የከተማ ቦታን በነፍስ ወከፍ ሸንሽኖ በስምሪት ያስያዘ እንደሆነ ሲታወቅ ፤ በተለይ በወታደራዊ መኮንንነት ስልጣን ላይ ለመደባቸው የትግራይ ተወላጆች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ 500 ካሬሜትርና ከዚያም በላይ ቦታ በስምሪት በማከፋፈል፤ የቤት መስሪያ ገንዘብና አሸዋ የሚያመላልስ የመንግሥት ጭነት መኪና በመመደብ አዳዲስ ባለሃብት እንዳደረጋቸው ይታወቃል። ይህ የአሁኑ አዋጅ አፈጻጸም እነዚህን አዳድስ ባለሃብቶች ያካትት አያካትት ለጊዜው የታወቀ ነገር ባይኖርም ፤ ባለፉት 20 አመታት በተደረገው የአገር ሃብት ዘረፋና በሙስና በተገኘ ሃብት አብዛኛው የወያኔ ሹሞች ተሳታፊ በመሆናቸው፡ ይፈጸምባቸዋል እንኳ ቢባል አሁን ከያዙት በተጨማሪ ሌሎች እጥፍ ቦታዎችን በሊዝ የራሳቸው ለማድረግ የሚያስችላቸው የገንዘብ አቅም አላቸው ተብሎ ይታመናል።

የዚህ የአዲሱ አዋጅ ዋናው አላማም በአገራችን የነበሩትን ነባር ሃብታሞችና የከተማ ቦታ ባለ ይዞታዎችን በአዳዲሶቹ የወያኔ ከበርቴዎችና ደጋፊዎቻቸው በመተካት ለዘመናት የፖለቲካውን ሥልጣን ለመቆጣጠር ያለው የረጂም ጊዜ ዕቅድ ወጤት አካል እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።

የግንቦት 7 ድምጽ የአገር ሃብትን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ሥር በማዋል ዜጎችን በገዛ አገራቸው ለዘመናት ባሪያ አድርጎ ለመግዛት እያሰሬ ያለውን የወያኔ አገዛዝ በተባበረ ትግል ለመጣል የሚደረገውን ትግል ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ እንዲቀላቀል ጥሪውን ያቀርባል።

### የጀርመን የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አባላት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በመጨረሻም ጀርመን ከኢትዮጵያ ጋር የጠበቀ የንግድ ግንኙነት እንዳላት ይታወቃል። ነገር ግን "ከኢትዮጵያ ጋር የቆየ ግንኙነት ስላለን ብቻ፤በአገሪቱ የሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ እየተፈፀመ ያለውን ነገር ችላ የምንለው አይደለም"ሲሉም አባላቱ ተናግረዋል።

አፋኙና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ እጅግ በርካታ ለሃገር ተቆርቁአሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንን፣ ጋዜጠኞችንና አክቲቪስቶችን እንዲሁም የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር አካላትን ሽብርተኞች ናችሁ፣ የሽብርተኛ ቡድን ደጋፊዎች ናችሁ በማለት ወደ እስርቤት ማጎሩ በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

### በቤልጂዩም የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የኢድ-አልፈጥርን በዓል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የበአሉ አዘጋጅ ኮሚቴ የዕለቱ ዝግጅት ከታላላቆቹ የእስልምና ሃይማኖቶ የበአላት ቀናት አንዱ የሆነውን ኢድ አልፈጥርን በጋራ ከማክበር የተለየ ፖለቲካዊ ይዘት እንደሌለው በማስረዳት ልኡካን ቡድኑን ለማረጋጋት ቢሞከርም እንዳልተሳካ የደረሰን ሪፖርት ያስረዳል።

በቦታው የተገኙት የንቅናቄያችን አመራር አባል ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት ወያኔ በራሳቸው እውቀትና ልምድ የሚተማመኑ ፤ በየትኛውም የመንግሥት ሥራ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው የሚሰጡት አገልግሎት ለአገራቸውና ለወገናቸው ጥቅም መሆኑን በሚገባ ለመረዳት አቅም ያላቸው ባለሙያዎችን ሆን ብሎ አንድ ባንድ ካባረረ በኋላ በሚከፈላቸው ደመወዝና በተመቻቸላቸው የአገር ሃብት ዘረፋ ሂሊናቸውን አደንዝዘው የታዘዙትን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ በሆኑ ዘመናዊ ሎሌዎች የተሞላ ድርጅት ለመሆኑ ይህ የብራስልሱ የወያኔ ኤምባሲ እርምጃ አሳይቶአል ብለዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org